DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ይህ የDCPS የተማሪ ከክፍል-ወደ-ክፍል ማለፊያ/Student Promotion ፖሊሲ፣ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ - በDCPS ከዚህ-ቀደም የታወጁትን ፖሊሲዎች፣ ሜሞራንደም እና/ወይም መመሪያዎችን - ይሽራል እና ይተካል።

**ቻንስለሩ ያጸደቁት: በስራ-ላይ የዋለበት ቀን:**
ከኦገስት (August) 13 ቀን 2018

# የDCPS የተማሪ ከክፍል-ወደ-ክፍል ማለፊያ/Student Promotion ፖሊሲ

## I. ዓላማ

ሁሉም ተማሪ የመወደድ ስሜት እንዲሰማው፣ ችግርን-ተቋቋሚነት ስሜት እንዲኖረው እና በአዎንታዊነት ተጽዕኖ የሚያደርግ ማህበረሰብ እንዲሆን ለማዘጋጀት እና ጠንካራና ሁሉን-አካታች የሆነ የመማሪያ አካባቢዎችን ለሁሉም ተማሪዎች በመስጠት - በሕይወታቸው እንዲበለጽጉ መደረጉን ለማረጋገጥ፤ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) በቁርጠኝነት ይሰራል። DCPS፤ ለሁሉም የማንነት-መለያዎች እና የብቃት-ችሎታ - የተማሪዎች እድገትን በማፋጠን ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ይህም - ዕድል ለማግኘት እና በመማር ላይ-የሚገኙትን እንቅፋቶችን ለማስወገድ - ፍትሃዊ-በሆነ ሁኔታ ማግኘት-መቻላቸውን በማረጋገጥ ነው። ይህ ፖሊሲ፤ የDCPSን - ለተማሪ ከክፍል-ወደ-ክፍል የመተላለፍ እና የመድገም/retention መስፈርቶችን ያቀርባል።

## II. ስልጣን/Authority[1]

| **ምንጭ/Source** | **ጥቅስ (Citation)** |
|---|---|
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ደንብ/Code of the District of Columbia | D.C. Code§§ 38-781.01 - 38-781.06 |
| ኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች/District of Columbia Municipal Regulations (የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools) | 5-E DCMR §§ 2200 - Reporting 5-E DCMR § 2201 |

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጓሜዎች/Definitions

A. **ቻንስለር:** የDCPS ዋና-ስራ አስፈፃሚ ሹም፣ በዲሲ ኮድ/DC Code §38-174.[2] በተመሠረተው-መሠረት

B. **ዋና የትምህርት-ዓይነት ዙሪያዎች:** የንባብ/ቋንቋ አርትስ/arts፣ ሂሳብ፣ ሣይንስ፣ እና ኅብረ ትምህርት/social studies።[3]

C. **የማለፊያ-የውጤት ደረጃ:** ለቅድመ መዋዕለሕጻናት (pre-K) እስከ 5ኛ ክፍል ላሉ፣ በትምህርት-ዓይነቱ ወይም በይዘት አካባቢው - የብቃት-ደረጃን ወይም የላቀ ውጤትን ማግኘት። ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ፣ ለኮርሱ ክሬዲትን ማግኘት።[4]

D. **ወደ-ሌላ ክፍል ማለፍ/Promotion:** ከpre-K እስከ 11ኛ ክፍል ላሉ፣ ለተማሪዎች - ወደሚቀጥለው የክፍል-ደረጃ ማለፍ።[5]

E. **መድገም/Retention:** ተማሪው የሚጠበቅበትን የማለፊያ መስፈርት-ባለማሟላቱ-ምክንያት፤ አሁን-ባለበት የትምህርት ቤት የክፍል-ደረጃ ውስጥ እንዲደርግም-ማድረግ/Repetition።[6]

F **የትምህርት ዓመት:** በኦገስት (August) ወር በሆነው በአንዱ-ዓመት ላይ ጀምሮ፣ በሚቀጥለው ዓመት ላይ የሚያልቀው የትምህርት ቤት ተርም/term። "የትምህርት ዓመት/school year" የሚለው-አባባል፣ የበጋ (summer) ትምህርት ቤትን-አያካትትም።[7]

G **የትምህርት-ዓይነት እና የይዘት ዓይነት-ዙሪያ:** የተወሰነ የኮርስ ጥናት/course of study፤ እንደ - ሂሳብ/mathematics፣ እንግሊዘኛ ቋንቋ አርትስ/English language arts፣ ጽሁፍ፣ ወይም ስነ-ጽሁፍ/literature.[8]

## IV. አስፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች

### A. አጠቃላይ መስፈርት/General Criteria

በሁሉም ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት ውስጥ - ወደሚቀጥለው የክፍል-ደረጃ ለማለፍ ከግምት-ውስጥ የሚገቡ ናቸው።[9]

---

[1] በዚህ ፖሊሲ ውስጥ፣ ምንም-ነገር - የፌደራል፣ የስቴት ወይም የአካባቢውን ሕግ - አይተካም።
[2] DC Code§ 38-781.01.1.
[3] 5-EDCMR § 2201.6 (a).
[4] DC Code§ 38-781.01.5 (A) (B).
[5] DC Code§ 38-781.01.8.
[6] DCCode§ 38-781.01.10.
[7] DC Code§ 38-781.01.11.
[8] DC Code§ 38-781.01.12.
[9] 5-EDEMR-§-2-WI.,____________

ወደሚቀጥለው-ክፍል ለማለፍ፤ ተማሪዎች በሁሉን **ዋና የትምህርት-ዓይነት ዙሪያዎች - ማለፍ/pass** አለባቸው። ወደ ሌላ ክፍል-ማለፉ ከመከናወኑ በፊት፣ ውሳኔውን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ-መግለጫን ርዕሰ-መምህሩ - ለቻንስለሩ ካልፃፉ-በስተቀረ፣ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ፣ ከ30 ቀናት በላይ ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) ያላቸው የDCPS ተማሪዎች - ወደሌላ-ክፍል መዛወር የለባቸውም።[10]

### B. ከPre-K – 8ኛ ክፍል - ለሆኑ ተማሪዎች - ወደሌላ-ክፍል መዛወር እና መድገም (Promotion and Retention)

በዲሲ ኮድ/DC Code § 38-781.02 መሠረት፤ ከቅድመ መዋዕለ-ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ውስጥ የተመዘገቡ የDCPS ተማሪዎችን - ወደ-ሌላ ክፍል የማዘዋወር እና የመድገም ውሳኔን በተመለከተ፣ በተማሪው አስተማሪ በተሰጠው-አስተያየት እና በDCMR ውስጥ በተቀመጡት ወደሌላ-ክፍል የማለፍ/promotion - መስፈርቶች መሠረት፣ በተማሪው ርዕሰ-መምህር የሚወሰኑ ናቸው። በDCMR ውስጥ የመዛወሪያ መስፈርቶችን የማያሟሉ ማንኛውንም ተማሪ፣ እንዲደገም ለማድረግ ርዕሰ መምህሩ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሆኖም-ግን፣ ርዕሰ-መምህሩ ወደ-ሌላ ክፍል ማለፉ ከመደረጉ በፊት፣ ለቻንስለር - የጽሁፍ ማብራሪያ እስከሚያቀርቡ ድረስ፣ ርዕሰ-መምህሩ እንደዚህ ዓይነቱን ወደ-ሌላ ክፍል የማለፍ መስፈርቶችን የማያሟላ ተማሪን - ወደ-ሌላ ክፍል ማሳለፍ ይችሉ-ይሆናል።

እንደ 5-E DCMR § 2201.6 መሠረት፤ ከpre-K እስከ 8ኛ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች - ወደሚቀጥለው የክፍል-ደረጃ ለመዘዋወር-እንዲችሉ፣ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:

- ብቃት-ያለው ወይም የላቀ-ደረጃ ያለው ማርኮች (marks)ን በዋናው የትምህርት ዓይነቶች በሆነው - በንባብ/የቋንቋ ስነጥበባት (Language Arts)፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ እና የኅብረ ትምህርት (Social Studies) ማግኘት፤ እና በሚያስፈልግ ጊዜ፣ የገጠሙ-ችግሮች ላይ የጣልቃ-ገብነት የመማር ዕቅድ ስኬት ላይ የመድረሻ ግቦችን፣ እና
- በመማሪያ ዘዴው በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) ፖሊሲ ጋር የመታዘዝ መስፈርቶችን ማሟላት ነው።

*ማስታወሻ:* በpre-K ወይም በመዋዕለህፃናት ውስጥ የሚገኝ ተማሪ፣ በዋና-ዋና የትምህርት-ዓይነት ዙሪያዎች፣ የብቃት-ደረጃ መስፈርቶችን ያሟላ-ከሆነ፣ ነገር-ግን፣ በአስተማሪው ወይም በወላጅ - ወደ መዋዕለሕፃናት ወይም 1ኛ ክፍል ለማለፍ ዝግጁ-ሆኖ ካልተገኘ፤ በአካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት መስኮች በተግባራዊ-ችሎታዎች ደረጃ - የpre-Kን ወይም መዋዕለህፃናትን - እንደመድገም/retention ሳይመደብ፣ በድጋሚ-ለመማር አማራጭ ሆኖ ከግምት-ውስጥ ሊገባ ይችላል።

### C. ከ9ኛ – 11ኛ ክፍል-ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ ወደሌላ-ክፍል ማለፍ እና መድገም/Promotion and Retention

በዲሲ ኮድ/DC Code § 38- 781.02 መሠረት፣ ከ9ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ውስጥ ተመዝግበው-የሚማሩ የDCPS ተማሪዎች፣ በ5-E DCMR § 2201.8 የተቀመጠውን (ከታች-የቀረበውን) ተማሪው ከክፍል-ወደ-ክፍል የማለፍ መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ፣ የሚያልፍ-ይሆናል። በDCMR ውስጥ የመዛወሪያ መስፈርቶችን የማያሟሉ ማንኛውንም ተማሪ፣ እንዲደገም ለማድረግ ርዕሰ መምህሩ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሆኖም-ግን፣ ርዕሰ-መምህሩ ወደ-ሌላ ክፍል ማለፉ ከመደረጉ በፊት፣ ለቻንስለር - ወደሌላ-ክፍል ለመዛወሩ አሳማኝ-የሆነውን የጽሁፍ ማብራሪያ እስከሚያቀርቡ ድረስ፣ ርዕሰ-መምህሩ እንደዚህ ዓይነቱን ወደ-ሌላ ክፍል የማለፍ መስፈርቶችን የማያሟላ ተማሪን - ወደ-ሌላ ክፍል ማሳለፍ ይችሉ-ይሆናል።

እንደ 5-E DCMR § 2201.8 መሠረት፣ ተማሪዎች የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የምርቃት (graduation) መስፈርቶችን፣ በካውንስለራቸው በተፈረመው እና በተፈቀደው የምርቃት (graduation) መስፈርቶችቸውን ለማጠናቀቅ በየግል የምርቃት ዕቅድ ላይ እንደሚያስፈልጋቸው ጊዜ እና እርዳታ አኳያ፣ በሶስት-፣ አራት-፣ ወይም አምስት-ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያጠናቅቁ ይችላሉ። የሚከተሉት መመሪያዎች፣ የደረጃ (grade) መግለጫ በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ለፈተና ሂደት ማከናወኛነት ጥቅም ላይ ይውላል:

- የ9ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ ክፍሎችን (units) ጨምሮ፣ ስድስት የ'Carnegie Units'ን በማግኘት የሚያስፈልጉት ኮርሶች - የ'content standards'[11] በማጠናቀቅ ያገኘ ማንኛውም ተማሪ፤ እንደ 10ኛ ክፍል ተማሪ[12] ሆኖ ለመመደብ ብቁ ይሆናል።

- የ10ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ እና የአልጄብራ (Algebra) Iን ጨምሮ፣ ማንኛውም የ'content standards'ን በማጠናቀቅ፣ ከሚያስፈልጉ ኮርስች ውስጥ 12 'Carnegie Units' ያገኙ ማንኛውም ተማሪ፤ እንደ 11ኛ ክፍል ተማሪ ሆነው ለመመደብ ብቁ ይሆናሉ።

---

10 DC Code § 38-781.02(c)(2).

11 የይዘት ደረጃዎችን የማሳካት (Achievement of content standards) ሁኔታ፣ በ5-E DCMR § 2200.7 መሰረት የማለፊያ-ማርክ (passing mark)/የደረጃ-ውጤት በማግኘት ላይ የተመሰረተ ነው።

12 ማስታወሻ፤ በ5-A DCMR § 2203.3(d) ውስጥ-የሚጠቅሰውን፤ ትምህርት ቤቱ ለመተው/waiver-ለማድረግ - ካልተፈቀደ-በስተቀር፤ ሁሉም ተማሪዎች ከ2016-2017 የትምህርት ዓመት ጀምሮ - ከአስረኛ (10ኛ) ክፍል በፊት-ባለው ጊዜ፣ በ'አልጄብራ/Algebra 1' መመዝገብ አለባቸው።

- የ11ኛ ክፍል እንግሊዘኛ/Englishን ጨምሮ፣ ማንኛውም የ'content Standards'ን በማጠናቀቅ፣ ከሚያስፈልጉ ኮርሶች ውስጥ 18 'ካርኔጊ ክፍሎች/Carnegie Units' ያገኘ ማንኛውም ተማሪ፤ እንደ 12ኛ ክፍል ተማሪ-ሆነው ለመመደብ ብቁ ይሆናሉ።

### D. ወደ-ሌላ ክፍል ማለፍ እና መድገብ/Promotion and Retention: ሁሉም የDCPS ተማሪዎች

እንደ ዲሲ ኮድ § 38-781.02(c)(2) መሠረት፣ መዛወሩ ከመካሄዱ በፊት፣ ርዕሰ መምህሩ ውሳኔው ትክክል እንዳልሆነ፣ ለቻንስለሩ የጽሁፍ ማብራሪያ ስካላቀረቡ ድረስ፤ ከ30 ቀናት በላይ ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ያለው ማንም ተማሪ መዛወር የለበትም።

እንደ 5-E DCMR § 2201.4(a) መሠረት፤ በበርካታ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ሁሉን-አቀፍ ምልከታ ካልኖረ እና ተማሪው የሚማርበትን ትምህርት ቤት አጠቃላይ-የሆነ ስልጣን-ያለው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ ካልተፈቀደ-በስተቀር፤ ተማሪው በDCPS ተመዝግቦ-በሚማርበት ወቅት-ላይ፣ ከአንድ ጊዜ በላይ መድገም አይችልም።

ተማሪው ወደ-ሌላ ክፍል ለማለፍ - ሁሉንም መስፈርቶች ካላሟላ፣ ነገር-ግን ተማሪው ቀደም ብሎ በመድገሙ ምክንያት - ወደ መካከለኛ-ደረጃ ወይም ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የሚሄድ-ከሆነ፤ ርዕሰ-መምህሩ ሁሉንም ያልተሟሉ መስፈርቶችን የሚገልጽ ሪፖርት ለተቀባዩ ትምህርት ቤት ማቅረብ አለበት።[13] ይህ ሪፖርትእስከ ጁን (June) 30 ድረስ እንዲቀበሉት-መደረግ ያለበት እና ለበጋ (summer) ትምህርት ቤት በሚዘጋበት-ጊዜ፣ አዲስና-ማሻሻያው/update መደረግ-አለበት። ከትምህርት ዓመቱ መጨረሻ በፊት ወደሌላ-ለሚሄዱ ተማሪዎች፤ ሪፖርቱ ተማሪው በትምህርት ቤቱ ከተመዘገበ በ30 የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለተቀባዩ ትምህርት ቤት መቅረብ አለበት። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፤ በተቀባዩ ትምህርት ቤት ውስጥ - በድጋፍ አገልግሎቶች/support services ውስጥ ይመዘገባሉ።

### E. የይግባኝ-አቤቱታዎች ሂደት/Appeals Process

እንደ ዲሲ ኮድ § 38-781.04 መሠረት፣ ተማሪው ወይም ወላጅ - በመድገሙ ውሳኔ ላይ ካልተስማሙ፤ ወደ ትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ - በውሳኔው ላይ ያላቸውን አቤቱታ በጽሁፍ በመግለጽ የማስገባት-መብት አላቸው።

በውጤቶች-ደረጃዎች ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች፤ በDCPS የውጤት-ደረጃ አሰጣጥ ፖሊሲ/DCPS Grading Policy እና 5-E DCMR § 2602 ውስጥ የተዘረዘሩትን - የይግባኝ-አቤቱታ ሂደት እና የጊዜ-አቀማመጦችን፣ መከተል አለባቸው። ፈቃድ-ባላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) ምክንያት የሚደረግ የይግባኝ-አቤቱታ፣ በDCPS መመሪያዎች እና በ5-E DCMR §§ 2103.7 እስከ 2103.19 የተዘረዘሩትን ሂደቶች እና የጊዜ-አቀማመጦችን መከተል አለባቸው፤ ሆኖም-ግን፣ የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ - በ5-E DCMR § 2103.9 የሚጠይቀውን የምልከታ-ማድረጊያ ፓናል/review panelን - ይሰበስባል።

### F. የመድገም (Retention) እና ወደሌላ-ክፍል የማለፍ (Promotion) ውሳኔዎች-ላይ የሚገኙ ሰነዶች

1. የ'DCMR'ን ወደ ሌላ-ክፍል ማለፊያ/Promotion መስፈርትን-ለማሟላት ያልቻሉ ተማሪዎችን-ማስደገም

ርዕሰ-መምህሩ ተማሪው እንዲደግም ውሳኔ በሚያደርጉ-ጊዜ፣ ይህ ውሳኔ - በተማሪው የኤሌክትሮኒክ መዝገብ በሆነው በተማሪ መረጃ ሲስተም/Student Information system (SIS) ውስጥ-በሰነድነት-መቀመጥ አለበት። የውሳኔው መሠረታዊ-የሆነው ምክንያት፣ ተማሪው ያላሟላው የDCMR ወደሌላ-ክፍል የማለፊያ/promotion መስፈርቶች - በግልጽ-የሚያብራራውን ጨምሮ፣ በተማሪው የፋይል ስብስብ ውስጥ - መቀመጥ አለበት።

2. የ'DCMR'ን ወደ ሌላ-ክፍል ማለፊያ/Promotion መስፈርትን-ለማሟላት ያልቻሉ ተማሪዎችን - ወደሌላ-ክፍል ማሳለፍ

ርዕሰ-መምህሩ - ተማሪውን ወደሌላ-ለማሳለፍ በሚወስኑበት-ጊዜ እና/ወይም ወላጅ - በመድገም ውሳኔው ላይ ያቀረቡትን የይግባኝ-አቤቱታ ሲያሸንፉ፤ መሠረታዊ-የሆነውን ምክንያት ጨምሮ - የጽሁፍ ማረጋገጫን፣ ለትምህርት ቤቱ የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ፣ መቅረብ-አለበት። ወደ-ሌላ ክፍል ማለፉ/promotion ከመካሄዱ-በፊት፣ የማረጋገጫው ቅጂ - ወደ ቻንስለሩ ቢሮ መቅረብ-ያለበት እና የተማሪውን የፋይል ስብስብን - ያካተተ-መሆን አለበት።

### G. አስፈላጊ-የሆነ - በበጋ (Summer) ትምህርት ቤት

እንደ ዲሲ ኮድ § 38- 781.05 መሠረት፤ በ'DCMR' ውስጥ የተገለጹትን ወደሌላ-ክፍል የማለፊያ መስፈትን - ማሟላት-ባለመቻላቸው የደገሙ ተማሪዎች፤ በርዕሰ-መምህሩ ወይም በቻንስለሩ በተለየ-ሁኔታ ፈቃድ ካላገኙ በስተቀረ፣ እንዲደግሙ የተደረገበትን የትምህርት ዓመትን ተከትሎ ወዲያውኑ በበጋ (summer) ትምህርት ቤት ክፍለ-ጊዜ ውስጥ መማር-አለባቸው።

[13] ሪፖርት-ማድረጊያው፣ ተማሪውን ለማስደገም ብቁ-ሊሆኑ የሚችሉ አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎችን ማካተት አለበት፣ ይህም ከብቃቱ ጋር-ተያያዥ-የሆነ የቀለም-ትምህርት ደረጃን እና/ወይም በሚፈለገው የይዘት ዙሪያዎች ክሬዲት ማግኘትን፣ እና በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት መስፈርቶችን ማከበርን - አስፈላጊ-ሆኖ በሚገኝ ጊዜ፤ ያለውን አካትቶ-መያዝ አለበት።

በመድገም ምክንያት - በበጋ (summer) ትምህርት-ቤት ውስጥ ገብቶ-የሚማር ተማሪ፣ ተማሪው የሚከተሉትን መስፈርት ካሟላ - ወደሌላ ክፍል ለማለፍ እንደገና ይገመገማል:

- ከበጋ (summer) ትምህርት ቤቱ - ከሦስት በላይ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች - ከሌለው፤ እና
- ተማሪው፤ በትምህርት ዓመቱ የማለፊያ ነጥብ ባላስመዘገበት በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ወይም ይዘት ዙሪያ፣ የማለፊያ ነጥብ ይቀበላል።

የበጋ (summer) ትምህርት ቤትን ካጠናቀቁ-በኋላ፣ በDCMR ውስጥ የተቀመጠውን ወደሌላ-ክፍል የማለፍ መስፈርትን ያሟላ ተማሪ - እንዲያልፍ-የሚደረግ ይሆናል።

ከላይ በተጠቀሰው መመሪያ መሠረት፤ በበጋ (summer) ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲማሩ ከተለዩት ተማሪዎች በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ ርዕሰ-መምህር - በበጋ ትምህርት ቤት መመዝገቢያ የጊዜ-ገደቡ ከማለቁ በፊት - በበጋ (summer) ትምህርት ቤት ውስጥ ቢማሩ ጥቅም-ያገኙ ይችላሉ ብለው ርዕሰ-መምህሩ  የሚያምኑባቸውን የተማሪዎች ስም ዝርዝርን - ለቻንስለሩ ያቀርባሉ።

### H. ልዩ-ሆኖ ከግምት-ውስጥ የገቡ ነገሮች/Special Considerations

ከጉዳተኝነት-ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (Students with disabilities) - ከጉዳተኝነት-ጋር የሚገኙ ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (Individuals with Disabilities in Education Act (IDEA) 2004 ላይ-ተለይቶ በተቀመጠው መሠረት፤ በግቦች፣ አላማዎች፣ ማመቻቻዎች እና ማሻሻያዎች ላይ-መሠረት - በ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን ከተዘጋጁት እና ከተስማሙበት የይዘት ደረጃዎች ጋር በተዛመደ-ሁኔታ፣ ወደ-ሌላ ክፍል ለማለፍ ብቁ ናቸው። ለእንግሊዘኛ ቋንቋን ለሚማሩ (English Learners)፤ የመድገም ማንኛውም ውሳኔ፣ ከባለ-ብዙ ቋንቋ (bilingual)/እንግሊዘኛን-እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ (English Second Learner (ESL) አስተማሪ[14] ጋር በጥምረት-ይካሄዳል።

## V. ፖሊሲውን-ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት ያስፈልጋቸዋል። አፈፃጸሙን ለመደገፍ፣ የሚፈለጉትን እንቅስቃሴዎች እና የጊዜ-አቀማመጥን በዓመታዊ አሰራሩ መሠረት፤ ሁሉም ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ፣ ከርዕሰ መምህራኖች ይጠበቅባቸዋል።

የዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም፤ በመደበኛ የመረጃ ስብስብ (data) ምልከታዎች፣ የመዝገብ ናሙናዎች፣ ከስር-መሠረቱ ላይ-ያሉ ሰነዶች ላይ ምልከታ በማድረግ፣ እና እንደየ-አስፈላጊነቱ - ቦታዎችን መጎብኘት - እነዚህን ሁሉ ያካተተውን፣ በማዕከላዊ የበላይ ክትትል ሂደት አማካኝነት ተጠናክሮ ይካሄዳል።

ይህ ማዕቀፍ (framework)፣ ሁላችንም በአንድነት ቀጣይነት ያለው ማሻሻያዎችን እና አለመገዛትን-የሚከላከል ዘዴን እንድንገነባ ያረጋግጥልናል። ቁልፍ ለሆነ መመሪያ እና እርዳታን-ከጥያቄዎች፣ ከስልጠና ወይም ከማስፈጸም ጋር ለማግኘት-ከፈለጉ፣ እባክዎን dcps.dc.gov ጎብኙ።

DCPS፤ እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍህታዊ-እኩልነት፣ የላቀ-በላጭነት ባለው አሰራር፣ በግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል - ቁርጠኝነቱን ያሳያል። ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ጥሰቶች ናቸው ተብሎ በዚህ መመሪያ ውስጥ የታመነባቸው ነገሮችን ላይ፣ የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነው (Chief Integrity Officer)ን ለማነጋገር፤ የኦንላይን የመምራት (Referral) ቅጽን በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@dc.gov. ኢሜል መላክ።

---

[14] 5-E DCMR § 2201.3.